1ኛ ዓመት ቁጥር 7
1st Year No. 7

ባሕር ዳር ጥቅምት 3 ቀን 1988
Bahir Dar 13th October 1995

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P. O. BOX

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር 7/1988
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መንገዶች ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገጽ 4

CONTENTS

Proclamation No-7/1995
A Proclamation to Provide for the Establishment of Rural Roads Authority of the Amhara National Regional State
Page 4

አዋጅ ቁጥር 7/1988 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የገጠር መንገዶች ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የገጠር መንገዶችን አገልግሎት ማስፋፋት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማትን ለማፋጠን የሚኖረውን ከፍተኛ ሚና በመገንዘብ፤

አደጉን የመጣውን የክልሉን ሕዝብ የመንገድ አገልግሎት ፍላጎት ለማርካት ውጤታማና አስተማማኝ የመንገድ ሥራና ጥገና ተግባር የሚያከናውንና በቦርድ የሚተዳደር የተጠናከረ የገጠር የመንገድ ሥራ ባለሥልጣን ማደራጀት በማስፈለጉ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ - መንግስት አንቀፅ 49/3/1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 7/1988 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

Proclamation No-7/1995
A Proclamation to Provide for the Establishment of Rural Roads Authority of the Amhara National Regional State

WHERE AS, realizing that the expansion of roads, to rural areas, has a great role in accelerating economic and social development;

WHERE AS , it has become necessary, in order to satisfy the growing needs of the people for road services, in the region , to organize a strong rural road constriction Authority which is to be managed by a board and carry out the construction and maintenance of dependable roads;

NOW, THERE FORE, in accordance with article 49/3/1 of the constitution of the Amhara National Region, the following is here by proclaimed.

PART ONE

GENERAL

1- Short Title
This proclamation may be cited as the "Rural Roads Authority of the Amhara National Regional State establishment proclamation No7/1995.

2. ትርጓሜ
የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-
1. "ባለሥልጣን" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መንገዶች ባለስልጣን ነው፡
2. "ቦርድ" ማለት የባለሥልጣኑ የሥራ አመራር ቦርድ ነው፡
3. " የገጠር መንገድ "ማለት ከአውራ ጎዳናዎችና ከከተማ መንገዶች ውጭ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ስሀገሪቱ በወጣው የገጠር የመንገድ ስታንዳርድ ሥር የሚጠቃለል መንገድ ነው፡

ክፍል ሁለት
ስለገጠር መንገድ ባለስልጣን መቋቋም፣ ድርጅታዊ አቋም፣ ስልጣንና ተግባር

3. መቋቋም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መንገድ ባለሥልጣን ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ አራሱን የቻለ መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

4. የባለሥልጣኑ ድርጅታዊ አቋም
1. ከተለያዩ መንግስታዊ አካላት የተውጣጣ የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. በክልሉ መንግስት የሚሾም አንድ ሥራ አስኪያጅና
3. አንዳስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መ/ቤቶችና ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

5. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሥልጣንና ተግባር
1. በክልሉ የገጠር መንገዶች ፊዚቢሊቲ ጥናት ያካሂዳል፣ የአጭር መካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
2. በክልሉ ውስጥ የገጠር መንገዶች ይሰራል፣ ያሻሽላል ይጠግናል፣ ወይም እንዲሰሩና እንዲጠኑ ያደርጋል፣
3. ለገጠር መንገዶች ሥራ የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችን ያዘጋጃል፣ አንዲዘጋጁ ያደርጋል፣
4. ለገጠር መንገዶች ሥራ ግንባታ ጥናት የሚያስፈልግ የሰው ሀይል፣ የገንዘብና የመሳሪያ አቅም ያዳራጃል፣ ያዘጋጃል፣
5. የገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን በተገባለት ውል መሰረት የጥራት ደረጃው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሰራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣
6. ከድርጅቱ የማንባታ አቅም በላይ የሆኑ የገጠር መንገድ ፕሮጀክቶች ለግል ሥራ ተቋራጮች ወይም ለመንግስታዊ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የሚሰጡበትን ሁኔታ እያጠና የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣
7. ለመንገድ ሥራና ጥገና የሚውል ጥሬ እቃና መሳሪያዎችን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ ያውላል፣ እንደሁም የተሻለ የማሽነሪዎች አደረጃጀት ይቀይሳል፣ ማሽነሪዎችን ይንከባከባል፣ ይቆጣጠራል፣
8. ለገጠር መንገድ ሥራ፣ ለጊዜያዊ መጠለያ፣ መሳሪያዎች ማከማቻና ሌሎች ለሥራው የሚያስፈልጉ መሬት፣ ድንጋይ ነክ ሃብት በነጻ ይጠቀማል፡፡ ሆኖም የሚገለገልበት መሬት ላይ ያረፉ ንብረቶችን በሚመለከት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሳ ይከፍላል፣
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፣
10. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፣
11. ሥራውን በሚመለከት በየሩብ ዓመቱ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሪፓርት ያቀርባል፡፡

ክፍል ሶስት
የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን የሥ/ዓመራር ቦርድ አባላት፣ ስብሰባ፣ተጠሪነትና ሥልጣንና ተግባር፣

6. የቦርድ አባላት
የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን የሥ/ዓመራር ቦርድ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰየም ... ሰብሳቢ
2. የሥራና ኮተማ ልማት ቢሮ ሃላፊ ... አባል
3. የትራንስፖርት ቢሮ ሃላፊ ... አባል
4. የገንዘብ ቢሮ ሃላፊ ... አባል

2- Definitions
Unless the context requires other wise, in this proclamation;
1- "Authority" means rural roads authority of the amhara national regional state;
2- "Board" means the managing board of the authority;
3- "Rural Roads" means roads that give services to the public excluding highways and urban Roads; which are incorporated under the standard set for rural roads in the country;

PART TWO
Establishment, Organizational Structure, Powers and Duties of the Rural Roads Construction Authority

3- Establishment
The Rural Roads Authority of the Amhara National Regional State here in after referred to as the "Authority" is here by established as an autonomous governmental institution under this proclamation;

4- Organizational Structure
The Authority shall consist of
1- A managing board constituted of different organs of the state;
2-A manager to be appointed by the regional state;
3- As may be necessary, it shall have branch offices and other staffs;

5- Powers and Duties of the Authority
1- Conduct feasibility studies of Rural Roads in the region; prepare short, medium and longterm plan and programme; and implement same , up on approval;
2- Undertake, or cause, the constructions, improvement, and maintenance of rural roads, in the region;
3- Prepare, or cause the preparation of designs, necessary for the construction of rural roads;
4- Prepare and organize manpower, financial and material capacity, necessary for the study and construction of rural roads;
5- Supervise and cause the supervision of rural roads construction, to ensure the accomplishment is in accordance with the quality of standard, time and cost limits, set for in the contract;
6- Submit recommendations, by studying the conditions for which rural road projects that are beyond the capacity of the authority, be given to private contractors or governmental construction authorities;
7-Conduct study and implement there of; organizations concerning the supply of raw materials and equipments necessary for rural road construction and maintenance, as well as, design better organization of machineries, handle properly and supervize the same;
8- Utilize free of charge, land , stone quarries and other materials, necessary for the purpose of rural road construction, temporary shelter, and equipment depot; However shall pay compensation in accordance withe the appropriate law, concerning the properties installed on the land used by the authority;
9- Own property, enter into contract, sue and be sued, in its own name;
10- Perform such other activities necessary for the execution of its objectives;
11- Submit, regarding its activity, quarterly performance report to the executive committee of the region;

PART THREE
Members, Meeting Procedures, Accountability, and Powers and Duties of the Managing Board of the Rural Roads Authority

6- Members of the Board
The managing board of the rural roads Authority shall have the following members

1- A person to be assigned by the executive committee of the regional state ... chairperson
2- Head of public Works and Urban Development Bureau ... member
3- Head of Transport Bureau ... member
4- Head of Finance Bureau ... member

5. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሃላፊ ..... አባል
6. የሰራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ ..... አባል
7. በክልሉ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመደቡ ሁለት ተወካዮች ..... አባላት
8. የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ..... ፀሐፊ
9. የሰራተኛ ተወካይ ..... አባል

7. የቦርድ ስብሰባ

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤
2. ከቦርዱ አባላት 2/3 ኛው በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓትና ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. ስለ ተጠሪነት

የቦርዱ ተጠሪነት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለርዕሰ - መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን የሥራ ዓመራር ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የባለሥልጣኑን የአጭር፤ የመካከለኛና የሪጅም ጊዜ እቅድ፤ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ገምግሞ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም አፈጸፀሙን ይከታተላል፤
2. የገጠር መንገዶችን በተመለከተ የፌዴራልና መንግስትና የክልሉን መንግስት ሕጎች፤ ደንቦች፤ ፖሊሲዎች፤ እና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡ ፖሊሲዎች ሕጎችና ደንቦች ያመነጫል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡፡
3. የባለስልጣኑን የየሩብ ዓመት፤ዓመታዊ የሥራ አፈጻፀምና የሂሳብ ሪፓርት ይገመግማል፤
4. የባለስልጣኑን ሥራ አስኪያጅ መርጦ ለክልሉ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስሾማል፤
5. ተጠሪነታቸው ለሥራ አስኪያጁ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፤ ምደባና ስንብት ያፀድቃል፤
6. የድርጅቱን የግንባታ አቅም ለማጠናከር የመሣሪያችና የተሽከርካሪዎች ግዥ ጥያቄን ይመረምራል፤ ከአስተያየቱ ጋር ለክልሉ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤
7. ከድርጅቱ የግንባታ አቅም በላይ የሆኑ ፕሮጀክቶች ለግል ሥራ ተቋራጮች ወይም መንግስታዊ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የሚሰጡበትን ሁኔታ ይወስናል፤
8. የባለስልጣኑ ሥራ አስኪያጅ የሚያቀርባቸውን ጉዳዩች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

ክፍል አራት
የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ሥ/አስኪያጅ ተጠሪነት ሥልጣንና ተግባር

10. የሥ/አስኪያጁ ተጠሪነት

የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ሥ/አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለክልሉ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤ለርዕሰ መስተዳድሩና ለቦርዱ ይሆናል፡፡

11. የሥ/አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባራት

የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ሥ/አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ ለባለስልጣኑ መ/ቤት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የሚያካትተውን ሲሆን በተጨማሪም፤ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የባለስልጣኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
2. የድርጅቱን የአጭር፤ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፤ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲያጸድቅም በተግባር ያውላል፤
3. የባለስልጣኑን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር ምደባና ስንብት በሚመለከት ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል፤
4. አግባብ ባለው ሕግ፤ በባለሥልጣኑ የአሠተዳደር ደንብና የሕብረት ስምምነት መሠረት ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያሳድጋል፤ ያስተዳድራል፤ያሰናብታል፤
5. ለባለስልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ እንደሆን ያደርጋል፤ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፤
6. ባለስልጣኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ የባለስልጣኑን መ/ቤት ይወክላል፤

7. የቦርዱን ውሳኔ ይፈጽማል፤ያስፈጽማል፤
8. የባለስልጣኑን መ/ቤት የየሩብ ዓመት፤ ዓመታዊ የሥራ አፈጻፀምና የሂሳብ ሪፓርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤
9. ሥ/አስኪያጁ ለኮሚሽኑ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በክፉል ለባለስልጣኑ ሌሎች

5- Head of Planning & Economic Development Bureau ..... member
6- Head of Labour & Social Affairs Bureau ..... member
7-Two persons to be assigned by the executive committee of the regional state ..... members
8- Manager of the Authority ..... secretary
9- Employees representative ..... member

7- Meeting of the Board

1- The regular meeting of the board shall convene once in every three months; However extraordinary meetings shall be held at any time, as may be necessary;
2- The presence of the majority members of the board, shall constitute a quorum;
3- Decisions of the board shall be passed by a simple majority vote. However, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
4- without prejudice to the provisions of this article, the board shall adopt its own rules and meeting procedures;

8-Accountability

The board shall be accountable to the executive committee and the Head of the regional state;

9- Powers and Duties of the Board

The managing board of the Rural Roads Authority shall have the following powers and Duties to:

1- Evaluate and submit short, medium, longterm plan and annual plan of action and budget to the executive committee, and upon approval follow up the implementation of same;
2- Ensure, the implementation of laws, regulations, policies and directives enacted by the Federal and the regional state concerning rural roads, and initiate policies, laws, and regulations, and upon approval implement same;
3-Evaluate quarterly and annual performance and financial reports of the Authority;
4- Select and present the manager of the authority for appointment, to the executive committee of the regional state;
5- Approve the employment, assignment, and dismissal of heads accountable to the manager ;
6- Examine, in order to strengthen the construction capacity of the authority, the purchase request for machinery and vehicles; and submit same together with its recommendation to the executive committee of the regional state;
7- Decide the conditions in which projects that are beyond the construction capacity of the authority be given to private contractors or governmental construction organizations;
8- Decide upon such other matters presented to it by the manager of the Authority;

PART FOUR
Accountability, Powers and Duties of the Manager of Rural Roads Authority

10- Accountability of the Manager

The Accountability of the manager of the Rural Roads Authority shall be to the executive committee, the Head of the Amhara National Regional state, and the managing board;

11- Powers and Duties of the Manager

The manager of the rural road authority shall ,in addition to the powers and duties vested in the authority, as enumerated under article 5 of this proclamation, have the powers and duties to

1- Direct, administer, and supervise, the activities of the authority;
2- Prepare and submit, to the board short, medium, long term plan, budget, and action plan of the authority, and upon approval implement same;
3- Submit, to the board for approval concerning employment, assignment, and dismissal, of heads of the authority;
4- Employ , promote, administer, and dismiss, its employees in accordance with the appropriate law, administrative regulation, and collective agreement of the authority;
5-Effect expenditure, in accordance with the approved budget and plan of action of the authority, and supervise the implementation of the same;
6-Represent the authority, in its dealings with other third parties;
7-Execute and cause the execution of the decisions of the board ;
8-Prepare and submit to the board, quarterly and annual activity performance and financial reports of the Authority;
9-Where the efficiency of the work of the authority necessitates so, the manager shall transfer his powers and duties partially by delegation to other heads and staffs, However, where the

ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።
ሆኖም ውክልናው ከ30 ቀናት የሚበልጥ ከሆነ
ሥ/አስኪያጁ ለሥ/አመራር ቦርድ በቅድሚያ በማቅረብ
ማስፀደቅ አለበት።
10. ለቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የባለስልጣኑ ሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር
1. የባለስልጣኑ ሰራተኞች ቅጥር በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፤
2. አንዳስፈላጊነቱ የባለስልጣኑን የሰራተኛ አስተዳደር ደንብ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

13. በጀት
የባለስልጣኑ በጀት፡
1. በመንግስት የሚመደብ፤
2. ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ ይሆናል።

14. የሂሳብ መዛግብት
1. ባለስልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የባለስልጣኑን የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝን በተመለከተ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አሰራርን ሊጠቀም ይችላል።

15. የሂሳብ ምርመራ
የባለስልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጪ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

16. የተሻሩ ሕጎች
ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

17. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ
ይህ አዋጅ በዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ጥቅምት 3 ቀን 1988 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት

manager deems it necessary to delegate powers and duties assigned to him for more than 30 days, shall present his request and cause to be decided by the board in advance;
10- Perform such other duties assigned to the board.

PART FIVE
Miscellaneous Provisions

12-Employment & Administration of the Staffs of the Authority
1-Employment of the staff of the authority shall be effected in accordance with labour proclamations;
2-The authority shall prepare employee administrative regulations of the authority, as may be necessary, and upon approval implement same.

13-Budget
The budget of the authority shall be:
1-Allocated by the state ;
2-Finance obtained from other sources.

14-Books of Accounts
1-The authority shall keep appropriate and complete books of accounts.
2-The board shall utilize, when it deems it necessary, accepted accounting procedures concerning the handling of the books of accounts and financial documents of the Authority .

15-Auditing
The books of accounts and financial documents of the Authority shall be audited by the Auditor General or external auditors assigned by the board.

16-Inapplicable laws
Any law which is inconsistent with this proclamation shall not apply to matters provided for in this proclamation.

17-Effective Date
This proclamation shall come into force on the date of its publication in the "Zikre-Hig" Gazzette

Done at BAHIR DAR
This 13th day of October 1995;
Council of the Amhara National Regional State.